# ጠ/ሚር መለስ እና ሲ.ኤን.ኤን (በተስፋ)

የታዋቂው የአሜሪካን የካቦ ቴሌቪዥን የለንደን ዜና መልህቅ ባለፈው ሳምንት ኢጋማሽ ላይ ለአቶ መለስ ዜናዊ ቃለመጠይቅ አድርጋላቸው ነበር:: ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ይህን ግንኙነት ያደረጉት በዳቮስ-ስዊዘርላንድ ላይ ለአለም የኢኮኖሚ መድረክ ውይይት በተገኙበት ወቅት በሳተላይት ግንኙነት ነበር:: የውይይቱ ከፊል ተጎርዶ በቴሌቪዥን ጣቢያው የአለም አቀፍ ድረገጽ ላይ ተለቅቆ አግኝቼ ለማየት እድል አግኝቼ ነበር:: ምንም እንኳን የተለቀቀው ክፍል አጭር ቢሆንም ጠያቂዋ የጠየቀችው ጥያቄ እና የአጠያየቋ ድምጸት ግሩም ሆኖ አግኝቼዋለሁኝ:: በጥያቄ እና መልሱም ያው የተለመደው የአቶ መለስ ብልጣብልጥነት ጎልቶ ይታያል(ለግል አስተያየቴ ከግርጌ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ):: ይህንን ጥያቄ እና መልስም ወደ አማርኛ መልሼ አቅርቤዋለሁኝ እነሆ::

**ጠ/ሚር መለስ**:-ሰራዊታችን ተተኪው የአሚሶም ወታደሮች እንደተገኙ እና ዝግጁ እንደሆኑ ሶማሊያን ለቆ ይወጣል::

**ሲ.ኤን.ኤን**:- ይህ ታዲያ መቼ ነው የሚሆነው?

**ጠ/ሚር መለስ**:- ይህ በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ሊከናወን ይችላል::

**ሲ.ኤን.ኤን**:- ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ሶማልያ ውስጥ ሰራዊቷን አስገብታ ነበር:: በወቅቱም ዘመቻው በውድቀት እንደተጠናቀቀ ይታወሳል:: እንደውም ብዙ የፖለቲካ ታዛቢዎች የኢትዮጵያ ሰራዊት **ጭራውን እንደውሻ ቆልፎ** በሽንፈት ሶማሊያን ለቆ እንደወጣ ይናገራሉ:: ይህኛው ዘመቻ ከበፊቱ በምን ይለያል?

**ጠ/ሚር መለስ**:- በአንቺ መደምደሚያ ላይ የግድ አልስማማም:: ይሁንና የአሁኑ ዘመቻ ልዩነቱ ብቻችንን አለመሆናችን ነው:: አሁን ከሶማሊያ ጊዜያዊ የሽግግር መንግስት እና ከአሚሶም ሰላም አስከባሪ ሰራዊት ጋራ በጋር ነው የምንሰራው:: አንዴ ከገባን አይቀር አካባቢውን ካጸዳን በኋላ የሶማሊያ ጊዜያዊ የሽግግር መንግስት ሰራዊት እና የአሚሶም ሰላም አስከባሪ ሰራዊት የተቀረውን ስራ ይሰራሉ::

**ሲ.ኤን.ኤን**:- የኢትዮጵያ ሰራዊት፣ ከኬኒያ እና ከሌሎች ሰራዊቶች ጋር አብራችሁ በመሆን አልሻባብን ያዳከማችሁ ይመስላቹኋል፤ ወይስ ሁኔታው ከዚህ የተለየ ነው??

**ጠ/ሚር መለስ**:- አልሻባብ በወታደራዊውም ሆነ በፖለቲካው መስክ በእጅጉን ተዳክሟል:: አሁን እየሰራን ያለነው ስራ እኔ እንደማስበው የተገኘውን ድል አጠናክረን የመግፋት ነው::

**ሲ.ኤን.ኤን**:- እርሶ እንደሚረዱት: አልሻባብ ከሶማሊያ የባህር ላይ ዘራፊዎች ጋር ግንኙነት ያለው ይመስልዎታል??

**ጠ/ሚር መለስ**:- እኔ የማውቀው የቀጥታ ግንኙነት የለም:: ነገር ግን ተደጋጋፊ እንደሆኑ አምናለሁ::

**ሲ.ኤን.ኤን**:- ግንኙነት አላቸው ነው የሚሉኝ??

**ጠ/ሚር መለስ**:- ግንኙነቶች አሉ:: የቀጥታ ብዬ ልጠራው የምችለው ግንኙነት እንዳላቸው ግን መረጃው የለኝም::

**ሲ.ኤን.ኤን**:- ትልቁ ፍራቻዎት ምንድነው? በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በሶማሊያ ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ያላት ትልቁ ስጋት ምንድነው??

**ጠ/ሚር መለስ**:- በጣም አስቸጋሪውን ወቅት የተሻገርነው ይመስለኛል.......

**ሲ.ኤን.ኤን**:- እንዴት እንደዚህ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል??

**ጠ/ሚር መለስ**:- ምክንያቱም አልሻባብ በማያዳግም ሁኔታ ተዳክሟል:: በወታደራዊ አቅሙም ብቻ ሳይሆን በፖለቲካውም ዘርፍ ጭምር፤ የ**ጨቋኝነታቸው** ደረጃ በቅርቡ በረሃብ የተጠቃውን የሶማሊያ ህዝብ ከኢአማኒ ለጋሾች ሰብዓዊ እርጥባን ከሚቀበሉ ይልቅ በረሃብ ቢሞቱ እንደሚሻላቸው ለማሳመን ያደርጉት በነበረው ቅስቀሳ ተጋልጧል:: ይህም ሊጓዙ የሚችሉበትን የ**ጭካኔ** ደረጃ ፍንትው አድርጎ አውጥቷል::

**ሲ.ኤን.ኤን**:- ኢትዮጵያ ራሷ በጣም ከፍተኛ ሊባል በሚችል **ቸነፈር**[i] የተጠቃችበት ወቅት ላይ ነው ያለችው:: ***የራሳችሁ ህዝብ በረሃብ እየተሰቃየ ባለበት ሁኔታ*** በምን መለኪያ በሶማሊያ ውስጥ የጦር ዘመቻ ማካሄዱ ምክንያታዊ ሊሆን ይችላል??

**ጠ/ሚር መለስ**:- በኢትዮጵያ ውስጥ **ቸነፈር** የለም።  በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰሩትን ሰብዓዊ ድርጅቶች ጠይቀሽ ልትረጂ ትችያለሽ። ከባድ ሊባል የሚችል ድርቅ አለ። የሆኖ ሆኖ ህዝባችንን ለመመገብ ዝግጁ ነን፤ ያም እንዳለ ሆኖ በሶማሊያ የምናካሂደው ዘመቻ ብዙ ብር የሚያስወጣን አይደለም።[ii]

---

[i]
**ቸነፈር** የሚለው ቃል ‘***famine***’ የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል ተክቼ ነው የተጠቀምኩት::

[ii]
ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ በኢትዮጵያ **ቸነፈር** እንደሌለ ለማሳመን እንደ እማኝ የጠሩት በአገሪቱ ውስጥ የሚሰሩትን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ነው:: ይህን ያደረጉበትም ምክንያት አላቸው:: እነኚህ ድርጅቶች እንደዚህ አይነት መረጃ አሳልፈው ለመስጠት በአገሪቱ ውስጥ ካላቸው ህልውና ጋር በተያያዘ እጅጉን ይቸገራሉ:: የመለስ መንግስት ቀይ መስቀልን እና ድንበር የለሽ የሃኪሞች ድርጅትን ከኦጋዴን ክልል በዚሁ ምክንያት እንዳስወጧቸው ካስታወሱ መልሱ በጣም ግልጽ ነው:: እንግዲህ የአቶ መለስ ብልጣ ብልጥነት እዚህ ላይ ነው:: የሰብዓዊ ድርጅቶችን አፍ በህግ በመመሪያ እና በቀላጤ ከሸበቡ በኋላ እነሱን መጠየቅ ትችላላችሁ ይላሉ::

ቃለ ምልልሱን በዩቱይብ ላይ ተለጥፎ አግኝቼዋለሁኝ በዚህ ማያያዣ ሄደው ይመልከቱት::

http://www.youtube.com/watch?v=P1lR2gwDoj8